# የአማራዉ ሕዝብ በስሙ እንዲነገድ አይፈቅድም፣ በኢትዮጵያዊነቱና በብሄራዊ አንድነቱ የሚኮራዉ ስደተኛ ለዘረኛ ከፋፋዮች አፍራሽ ሴራ አይንበረከክም

ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ / ብአዴን/ የተባለዉ ፀረ-ኢትዮጵያ የሃፍረት የለሽ አድርባዮችና የሆዳሞች ጥርቅም November 27, 2010 የ30ኛ እመት በዓሉን በለንደን እንደሚያከብር በኤምባሲዉ ድረ ገፅ አሳዉቋል።

ለመሆኑ የብአዴን አመሰራረት፡እንዴት እንደተቋቋመ፣ የመሪዎቹ ማንነት በመለስና በግብረ አበሮቹ በሚካሄደዉ ኢትዮጵያን የማጥፋትና የመበታተን ሴራ ምን ሚና እንደተጫወተና፣ በመጫወትም ላይ እንዳለ ለማንም ግልፅ ነዉ።
ኢህአዴግ የወያኔ መሪዎች ከአንድ ትግራይ የተዉጣጡ ጠባብ ብሄረተኞችና ዘረኞች ያልሆኑ ለማስመሰል ለማደናገሪያ የፈጠሩት ጭምብል ሲሆን ብአዴን ለዚህ ጭምብል ሽፋን እንዲሰጥ የአማራዉን ሕዝብ እንወክላለን በሚሉ እነመለስ ዜናዊ በመለመሏቸዉ ምንደኞች የተቋቋመ አስመሳይ ድርጅት ነዉ።

የብአዴን መሪዎችና ቅጥረኞች እንኳን የአማራዉን ሕዝብ እንባ ሊያብሱ ቀርቶ በታሪክ አጋጣሚ የወያኔ ዘረኛ ስርዓት ታማኝ አገልጋይነታቸዉ ለስልጣን ያበቃቸዉ የአማራዉ ሕዝብ ቀንደኛ ጠላቶች የሆኑ አልባሌ ግለሰቦች የተሰበሰቡበት ቡድን ነዉ።
ይሄ የህወሃት/ማሌሊት ግልገል (ተለጣፊ) ቡድን ላለፉት 20 ዓመታት በአማራዉ ህዝብ ላይ ለተሰሩት ወንጀሎች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተጠያቂ ነዉ። ለአካባቢዉ ህዝብ መብትና ጥቅም ከመቆም ይልቅ በተቃራኒዉ ዘረኛዉ የህወሃት/ማሌሊት አገዛዝ በአማራዉና በጠቅላላዉ ህዝባችን ላይ ከፍተኛ በደልና ስቃይ እንዲያካሂድ ምቹ ሁኔታን የፈጠረ፡የፈፀመና ያስፈፀመ ድርጅት ነዉ።
ከራሱ ከብአዴን በተለያየ ጊዜ የወጡ የአመራር አባሎች በተደጋጋሚ እንደመሰከሩት ድርጅቱም ሆነ መሪዎቹ የራሳቸዉ የሆነ ነፃነት የሌላቸዉ የመለስ ዜናዊ የህወሃት/ማሌሊት አመራር እንደፈለገዉ አሻንጉሊት አድርጎ የሚገለገልባቸዉ ዕቃዎች ናቸዉ።

በጣም የሚያሳፍረዉና የሚያስደንቀዉ ደግሞ የቡድኑ መሪዎች በወያኔ በራሱ ተመልምለዉ የተሰገሰጉትና አብዛኛዎቹ ከተለያየ ብሄረሰብ የተወለዱ መሆናቸዉ ነዉ። ለምሳሌ በረከት ስምዖን፣ ሕላዌ ዮስፍ፣ ተፈራ ዋልዋ የመሳሰሉትን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ የብአዴን መሪዎች ለአማራ ሕዝብ ያላቸዉን ከፍተኛ ንቀት በተለያየ ጊዜ በንግግራቸዉ በፅሁፋቸዉና በተግባራቸዉ በግልፅ ከማሳየታቸዉም በላይ የዘረኛዉ ወያኔ ቡድን ዓላማ በማስፈፀም ለብዙ የአማራ ሕዝብ ሕይወትና ንብረት አደጋ ላይ መዉደቅ አቢይ ምክንያት ሆነዋል።
ለዚህም ታምራት ላይኔ በሶማሌ፣ ተፈራ ዋልዋ በደቡብ ክልል ዉስጥ ያደረጓቸዉ ንግግሮች በታሪክ የማይዘነጉ ማስረጃዎች ናቸዉ።

*ሕወሃት/ማሌሊት በአሁኑ ጊዜ በአንድ ፓርቲ ጨቋኝ አገዛዝ አገሪቱን በሁሉም መንገድ ስለተቆጣጠረ በአምባገነንነት ለያዘዉ ስልጣን ሊያሰጋዉ የሚችለዉ በስደት ላይ የሚገኘዉ ኢትዮጵያዊ እንደሆነ በመገመት በአንድ ላይ እንዳይቆም ለመከፋፈል በርካታ አፍራሽ ስልቶችን በየጊዜዉ ይነድፋል።*
*ከነዚህም መካከል በዉጭ የሚገኘዉን ስደተኛ በመኖሪያ ቤት የመስሪያ ቦታና በሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ደልሎ መያዝ፡ በሌላም በኩል አንድነቱን ለመሸርሸር ዘርን መሰረት ባደረጉ የፓለቲካና የልማት እንቅስቃሴዎች ላይ ተሳታፊ እንዲሆን ለማድረግ መሞከር፡ እንዲሁም የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ያለ ለማስመሰል ታማኝ ተቃዋሚ ተብዮዎችን ለቅስቀሳ ማሰማራት ይገኙበታል።*
*ይህ ለአማራ ሕዝብ መብት፡ ጥቅምና ብልፅግና ሳይሆን ይልቁንም የአማራዉን ህዝብ በመርገጥና ብሄራዊ ክብሩን በማዋረድ፡ እንዲሁም ታሪካዊ ዳር ድንበሩን በእብሪት ሸንሽኖ ለሌሎች አሳልፎ በመስጠት የአማራዉን አንገት ለማስደፋት ለጠባብ የወያኔ መሪዎች ሎሌ የሆነዉን ተለጣፊ ድርጅት 30ኛ ዓመት በዓል ለንደን ላይ ለማክበር በዕብሪት የወጣዉ ዕቅድ በዉጭ የሚገኘዉ ስደተኛ በኢትዮጵያዊነቱ ያለዉን አንድነት ለመከፋፈል እንደሆነ ግልፅ ነዉ።*

*ይሁን እንጂ አንድም የአማራዉ ሕዝብ በስሙ እንዲነገድ አይፈቅድም፡ ሁለትም በኢትዮጵያዊነቱና በብሄራዊ አንድነቱ የሚኮራዉ በዉጭ አገር የሚገኘዉ ስደተኛ ለዘረኛ ከፋፋዮች አፍራሽ ሴራ እንዲህ በቀላሉ አይንበረከክም።*

*ስለዚህ ማንኛዉም ለሃገሩ ቀናዒ የሆነ የወገኑ በግፍ አገዛዝ ስርዓት መሰቃየት የሚቆጨዉና የሚያሳስበዉ ኢትዮጵያዊ ከነዚህ ከዘረኛዉ አምባገነንና ከግብረአበሮቹ ጎን በባንዳነት ተሰልፈዉ የቆሙ አድር ባይ ሆዳሞችና ወንጀለኞች በሚጠሩት ዝግጅት ላይ እንዳይገኝና በወገኖቹ ደም በተጨማለቀ ግብዣ ላይ ተሳታፊ እንዳይሆን ለማሳሰብ እንወዳለን። ይልቁንም ለአገሩ የሚቆረቆር ኢትዮጵያዊ ሁሉ ከሌሎች አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ጎን በመቆም እነዚህን የአገር አንድነትና የአማራ ህዝብ ጠለቶችን በፅኑ እንዲቃወምና በጋራ በመታገል የዘረኞችን የግፍ አገዛዝ ዕድሜ ለማሳጠር ተባብሮ እንዲሰራ ጥሪያችንን እናቀርባለን።*

*የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘረኝነትን በትግሉ ያስወግዳል!*
*የኢትዮጵያ አንድነት ለዘላለም ይኑር!*

*የኢትዮጵያዊያን ኔትዎርክ ለዲሞክራሲና ለፍትህ በለንደን*